የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party(EPRP)

ታህሣሥ 11 ቀን 2004 ዓ.ም

# ወያኔ ሀገር መሸጡን ገፍቶበታል

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሀገርን ለባዕድ መሸጥ ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡ ቻይናውም፣ ህንዱም፣ አረቡም ሌላውም ሁሉ የሀገራችንን መሬት እየተቀራመቱ ናቸው፡፡ ወያኔ የቋራን ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለግሶ እነሆ እስከዛሬ በከሀዲነት እየተወገዘ ነው፡፡

ይህ ክህደትና ሀገርን መጉዳቱ ሳይበቃ ወያኔ በቅርቡ ከሱዳን ጋር ባደረገው ስብሰባ የተፈረመው ስምምነት የሱዳን ዜጎች ሁሉ - ዘላኖቹን ጨምሮ - በነፃ ወደ ኢትዮጵያ መሬት የመዝለቅ መብትን ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህንን በባሕር ዳር ስብሰባ በትግራይ ክልልና በሱዳኖች መሀል የደራ ንግድ እንዲካሄድ ስምምነትን አፅደቋል፡፡ በአልፋሻጋና በምዕራብ ትግራይ መሀል ነፃ ንግድ መባሉም ተዘግቧል፡፡ የወያኔ ጦር ስደተኞችን በማሳደድ በአል ጋዲ በኩል ወደ ሱዳን ገብቶ እንዲንቀሳቀስም ሱዳን ፈቃድ ለግሷል፡፡ የሱዳን ዘላኖች፣ ከብት አርቢዎች፣ ...ወዘተ ወደ ኢትዮጵያ በነፃ ገብተው ይንቀሳቀሱ በሚል የተሰጠው ፍቃድ አንድም ሀገርን የሚያጠፋ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ነገ መሬቱም የእኛ ነው ብለው የሚሰየሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ ወያኔ ሀገርን መሸጥ ዋና ስምሪቱ ሆኖ ይገኛል፡፡ በገዳሪፍና አዋሳኝ የኢትዮጵያ ክፍሎች መሀል ግንኙነቱ በሁሉም መስክ ይስፋፋ የተባለውም ለኢትዮጵያ የሚበጅ አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በባህር ዳሩ ስብሰባ የተካፈለው የሱዳን ተጠሪ ያህያ ሀምዳዬን ሃሳበሲዶ እንደገለፀው በሱዳንና ወያኔ መሀል የፀጥታና ደህንነት ስምምነቱ ዋና ሲሆን ይህም ስምምነት ውጤታማ እንደሚሆን ይጠበቃል ተብሏል፡፡ የሱዳን አገዛዝ ኢትዮጵያዊ ስደተኞችን ለወያኔ አሳልፎ መስጠቱ በተደጋጋሚ የተዘገበ መሆኑም ይታወሳል፡፡ ወያኔ የሀገራችንን መሬትና ዜጎችንም ለሱዳን አሳልፎ እየሰጠ እያለ ሀገር ወዳድ ነን የሚሉ ሁሉ ዝምታን መምረጣቸው በጣም አነጋጋሪ ሆኗል፡፡

ኢሕአፓ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን መስጠቱን እያወገዘ በቅርቡ ወያኔና ሱዳን የተፈራረሙትን ስምምነትንም በጥብቅ ያወግዛል፡፡ ለሱዳን ዜጎች - ዘላኖች፣ አራሾች፣ ...ወዘተ በነፃ ግቡ ብሎ ፈቃድ መስጠቱ ሀገርን ለዝርፊያ አጋላጭ ነውናም ኢሕአፓ የሚቃወመውና የሚፃረረው ስምምነት ነው፡፡

በጋራና በቆራጥነት ሀገራችንን እናስከበር!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com